# የፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አፈፃፀም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ሚኒስቴር የዳግም ክትትል ሪፖርት

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

## የህግ ተገዢነት ዳግም ክትትል ሪፖርት

ጥር 2016 ዓ.ም.

# ማዉጫ


ምስጋና...... iiii

አህጽሮተ ሪፖርት ...... ivv

ምዕራፍ አንድ...... 0

ጠቅላላ መግቢያ...... 0

1.1 መግቢያ...... 0

1.2 የክትትሉ አላማ ...... 0

1.2.1 ጠቅላላ ዓላማ...... 0

1.2.2 ዝርዝር አላማ...... 0

1.3 የክትትል ስልት ...... 2

1.3.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ...... 2

1.3.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ...... 2

1.5 የክትትሉ ውስንነት...... 3

1.6 የሪፖርቱ አወቃቀር ...... 3

ምዕራፍ ሁለት ...... 4

መመሪያን ከማውጣት እና ከማስመዝገብ ሂደት አንፃር ...... 4

2.1 መመሪያን ስለማውጣት (አንቀጽ4)...... 4

2.2 መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ (አንቀጽ 5)...... 4

ሀ. መዝገብ ከማደራጀት አንጻር (አንቀጽ 7)...... 5

ለ. ማስታወቂያ ከማውጣት አንጻር (አንቀጽ 8)...... 5

ሐ. ለአስተያየት ለባለድርሻ ከመላክ አንጻር (አንቀጽ 9) ...... 6

መ. የውይይት መድረክ ከማዘጋጀት አንጻር (አንቀጽ10)...... 6

ሠ. የመመሪያ ይዘት ከማሟላት አንጻር (አንቀጽ 15) ...... 7

ረ. መመሪያን ለፍትህ ሚኒስቴር አስተያየት ከመላክ አንጻር (አንቀጽ 12)...... 7

ሸ. መመሪያዎችን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር (አንቀጽ 17)...... 7

ምራፍ ሦስት ...... 8

አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት ዳሰሳ...... 8

3.1 አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመስጠት አንፃር የታዩ ግኝቶች ...... 8

ሀ. የአስተዳደራዊ ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ...... 8

ለ. ጉዳይን ከመስማት አንጻር (አንቀፅ 28)...... 9

ሐ. በቅሬታ ላይ ውሳኔውን ለተገልጋይ ከመስጠት አንጻር (አንቀጽ 46) ...... 10

3.2 ቅሬታን በይግባኝ ከማየት አንፃር..............................................................11

ሀ.ቅሬታን የማቅረብ መብት ከማክበር አንፃር.................................................. ....11

ለ. ቅሬታውን ከመመርመርና ከመወሰን አንጻር ..................................................13

ሐ. በቀረበ ቅሬታ ላይ ውሳኔውን ለተገልጋይ ስለማሳወቅ..........................................13

ምዕራፍ አራት..............................................................................................14

ማጠቃለያ እና ምክረ ሀሳብ...................................................................................14

4.1 ማጠቃለያ..............................................................................................14

4.2. ምክረ ሀሳብ............................................................................................15

አባሪ አንድ ፡ በክትትሉ የተዳሰሱ ዋቢ ሕጎች.........................................................16

አባሪ ሁለት፡ መመሪያ ለማውጣት ስልጣን የሚሰጡ የአዋጅ ድንጋጌዎች ዝርዝር ......................18

አባሪ ሶስት፡ በክትትሉ የታዩ ሌሎች ሰነዶች..........................................................18

አባሪ አራት፡- የሚኒስቴሩ ተቋማዊ አደረጃጀት መግለጫ ..............................................19

አባሪ ስድስት፡ አዋጁ ከወጣ በኋላ የወጡ እና ያልተመዘገቡ ለናሙና የተጠቀምንባቸው መመሪያወች ዝርዝር፤ (ጅምር በመረቂቅ ላይ ያሉ)..........................................23

አባሪ ሰባት፡ ለናሙና የተመለከተናቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ዝርዝር..................................23

አባሪ ዘጠኝ፡ ቃለ- መጥይቅ ያደረግንላቸው እና መረጃ የሰጡን የሥራ ኃላፊዎች ዝርዝር ...........25

አባሪ አስር፡- የቃለ- መጠይቅ ጥያቄዎቸ...............................................................25

# ምስጋና

የሚኒስቴሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች አስፈላጊዉን መረጃ በመስጠት ላደረጉልን የሥራ ትብብር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. በፍትህ ሚኒስቴር ስም የላቀ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# አህጽሮተ ሪፖርት

*ይህ የዳግም ክትትል ሪፖርት ከዚህ በፊት በጤና ሚኒስቴር የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አተገባበር ላይ ከጥቅምት እስከ ታህሳስ ወር 2014 ዓ.ም ድረስ በተደረገው ክትትል መነሻ የቀረበ ሲሆን ዓላማውም በቀድሞ የክትትል ሪፖርት የተሰጡት ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ስለመደረጉና አለመደረጉ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ፡፡*

*በክትትሉ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የናሙና አወሳሰድን በተመለከተ የመረጃውን አግባብነት እና ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ቁልፍ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲያስችል አላማ መር (purposive sampling) ዘዴ ተመርጧል፡፡ በዚሁ አግባብ 12 የሚሆኑ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች በመምረጥ ቃለ መጠይቅ ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔ ናሙናዎችን በዘፈቀደ በመምረጥ ታይቷል፡፡*

*በተደረገው የዳግም ክትትል የተቋሙ የበላይ አመራሮች ለአዋጁ አፈጻጸም ልዩ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆኑን፣ በአዋጁ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር የተከናወነ መሆኑ እና የሕግ ክፍሉ የአዋጁን አፈፃፀም የማስተባበር ተግባር የተሰጠው ከመሆኑ አንጻር በዚህ ረገድ ቀድሞ የተሰጠው ምክረ ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መደረጉ ታይቷል፡፡*

*የመጀመሪያ ክትትል ከተደረገ በኋላ የፀደቀ መመሪያ ባይኖርም ከመመሪያ አወጣጥ አንፃር በረቂቅ ደረጃ ያሉ መመሪያዎች በተመለከተ መዝገብ አለመደራጀቱ፣ ማስታወቂያ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ አለመውጣቱ፣ ለባለድርሻ አካላት ለአስተያየት አለመላኩ እንዲሁም የህዝብ ውይይት የሚመለከታቸውን አካላት ብቻ በመጥራት ማካሄዱ ከአዋጁ አላማ እና መንፈስ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ በቀድሞ ክትትል እንዲሻሻል ምክረ ሀሳብ የተሰጠበት ቢሆንም ያልተሻሻለ መሆኑ ተመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል ማስታወቂያ በተቋሙ ድረ-ገፅ ላይ መውጣቱ በዚህ ረገድ መሻሻል መኖሩ ያመላክታል፡፡ በተመሳሳይ በፍትሕ ሚኒስቴር የተመዘገቡ ሁሉንም የተቋሙ እና የተጠሪ ተቋማት መመሪያዎች በተደራጀ መልኩ ለዚህ አላማ የተዘጋጀ ድረ-ገጽ በመፍጠር አለመጫኑ አሁንም በክፍተትነት ተመላክቷል፡፡ ሆኖም የተዘጋጁት መመሪያዎች እንዲኖራቸው የሚጠበቅ ይዘትን አሟልተው መገኘታቸው የተሻሻለ አፈፃፀም ተደርጎ ተወስዷል፡፡*

*አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ አንፃር የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ አቀራረብ በጽሑፍ ሆኖ በአካል፣ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊቀርብ መቻሉ፣ ጉዳይ በአግባቡ መሰማቱ፣ የአስተዳደር ውሳኔም ሆነ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ ይዘቱን የጠበቀ ውሳኔ ለተገልጋዩ መሰጠቱ በጥንካሬ ታይቷል፡፡ ማረጋገጫ ከመስጠት አንጻር ማረጋገጫው አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑንና ከአቤቱታው ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ዝርዝር የሚያሳይ አለመሆኑ፣ ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ቢያቋቁምም ማቋቋሙን ለተገልጋዮች ይፋ አለማድረጉ በቀድሞ ምክረ ሀሳብ መሰረት ሳይሻሻል የቀረ መሆኑ ግኝቱ ያመለክታል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# ጠቅላላ መግቢያ

## 1.1 መግቢያ

የጤና ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 እና 35 መሠረት ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በተጨማሪ በአንቀጽ 95 መሠረት በስሩ ስምንት ተጠሪ ተቋማት እና አምስት ሆስፒታሎችን በበላይነት የሚመራ ሲሆን በሕግ የተጣለበትንም ተግባርና ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችለውን መመሪያ የማውጣትና አስተዳደራዊ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን እንዳለው ይታወቃል፡፡

የጤና ሚኒስቴር በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችለውን መመሪያ ሲያወጣ፣ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሲሰጥ እና በሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የቅሬታ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ በተመለከተ የፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012ን የተከተለ ስለመሆኑና ስላለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6/6/ የፌዴራል ሕጎችን አፈጻጸም እንዲከታተል ለፍትሕ ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከዚህ ቀደም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአዋጁ አተገባበር ላይ በተደረገው ክትትል ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚገባቸው ምክረ ሀሳቦችን ሰጥቷል ፡፡ በዚሁ መሠረት የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ይህ ዳግም ክትትል ሊካሄድ ችሏል፡፡

## 1.2 የክትትሉ አላማ

### 1.2.1 ጠቅላላ ዓላማ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመመሪያ አወጣጥና አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እንዲሁም የቅሬታ አፈታት ሂደት በተመለከተ ቀደም ሲል በአዋጁ መሠረት እንዲፈጽም የተሰጠውን ምክረ ሀሳብ ተግራዊ መድረጉን ለመዳሰስ ነው፡፡

### 1.2.2 ዝርዝር አላማ

በዚህ ዳግም ክትትል:-

- ✓ በመጀመሪያ አፈፃፀም ክትትል ወቅት አዋጁን ከመፈፀም አንፃር የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች አተገባበር ያለበትን ደረጃ ለመለየት፣
- ✓ የምክረ-ሀሳብ አተገባበር ላይ የታዩ ክፍተቶች መለየት እና ካሉ ምክንያታቸውን በመለየት መፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡

## 1.3 የክትትል ስልት

### 1.3.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለዚህ ዳግም ክተትል የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህ የመረጃ ምንጮች ከዚህ በታች በዝርዝር የተመለከቱት ናቸው፡፡

**ሀ. የሕጎች ዳሰሳ**

ለተቋሙ ስልጣን ሰጪ ሕጎች፣ የተጠሪ ተቋማት ማቋቋሚያ ደንቦች እና ሌሎች ተዛማጅ ሕጎች ተዳሰዋል፡፡ እነዚህም የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014፣ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011፣ ሀገር አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤትና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 276/1994፤ የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 529/2015 እና ሌሎች ተያያዥ ሕጎች ተዳሰዋል፡፡

**ለ. ቃለ መጠይቅ**

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተዘጋጀው የቃለ-መጠይቅ ቼክሊስት መሰረት 12 ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ ተደርገዋል፡፡

**ሐ. የሰነድ ማስረጃዎች**

የ2015 ዓ/ም የመልካም አስተዳደር ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና የቅሬታ ማስተናገጃ የትንታኔ ሪፖርት፤ የተለያዩ አስተዳደራዊ ውሳኔ ናሙናዎች፣ በረቂቅ ደረጃ ያሉ አምስት መመሪያዎች፣ የዜጎች ስምምነት ሰነድ፣ የተገልጋዮች ቅሬታ ማቅረቢያና መልስ መስጫ ቅጻ ቅጾች ለክትትሉ እንደመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡

**መ. ምልከታ**

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አገልግሎት አሰጣጡን ለተገልጋዮች ግልጽ ከማድረግ አንጻር በቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ህንጻ መግቢያ ላይ አገልግሎት የሚሰጡ የስራ ክፍሎች አቅጣጫ መጠቆሚያ ስለመኖሩ ወይም አለመኖር ምልከታ ተደርጓል፡፡

### 1.3.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ

ለክትትሉ አስፈላጊና ጠቃሚ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲያስችለን አላማ መር (purposive sampling) የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተመርጧል፡፡ በዚሁ መሠረት የሴቶችና

የተለዩ አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ኃላፊ፣ የሥነ ተዋልዶ ጤና አማካሪ፣ የእናቶችና ጤና ከፍተኛ ባለሙያ፣ የሕግ አገልግሎት መሪ ሥራ-አስፈፃሚ ፣የሕግ ባለሙያዎች ፣የጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ፣ የሜዲካል አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ የሆስፒታልና ዳግኖስቲክ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ኃላፊ፣ የተቋማዊ ለውጥ ሥራ አስፈፃሚ እና የቅሬታና አቤቱታ ቡድን መሪ፣ የፌዴራል የጤና ባለሙያዎች ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ፀሐፊ ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርገዋል። እንዲሁም ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት ጋር በተያያዘ በዘፈቀደ የተመረጡ 33 የውሳኔ ናሙናዎች ከአዋጁ አንፃር ተመርምረዋል። ተያያዥ የሰነድ ማስረጃዎች ታይተዋል።

### 1.3.3 የመረጃ ትንተና ዘዴ

በቃለ መጠይቅ እና ሰነዶችን በመጠቀም የተገኘውን የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ከአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ መሰረት ከተዘጋጁት የአፈጻጸም ቼክሊስት መለኪያ ጋር በማነጻጸር ገላጭ (discripitive) በሆነ መንገድ ሪፖርቱ ተተንትኗል።

## 1.4 የክትትሉ ወሰን

ይህ ክትትል የመጀመሪያው ሪፖርት ከወጣበት ታህሳስ 2014 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2016 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የተከናወነውን አፈፃፀም የሚሸፍን ሲሆን ክትትሉ ተጠሪ ተቋማትን አላካተተም። በተጨማሪም ክትትሉ ከአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈፃፀም የሚዳስስ እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ሥልጣንና ተግባር አፈፃፀም የሚሸፍን አይደለም።

## 1.5 የክትትሉ ውስንነት

ከአስተዳደራዊ ውሳኔ ጋር በተያያዘ ሁሉንም ውሳኔዎች ማየት ያልተቻለ ቢሆንም የተለያዩ የውሳኔ ዓይነቶች በመውሰድ የተቋሙን አሰራር ለማየት ተሞክሯል።

## 1.6 የሪፖርቱ አወቃቀር

ይህ የዳግም ክትትል ሪፖርት በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የዳግም ክትትሉን አላማ፣ የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን ዘዴን፣ የዳግም ክትትሉ ወሰን እና ውስንነቶች የተገለጸበት ነው። በሁለተኛው ምዕራፍ የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የተዳሰሰበት ነው።

በሦስተኛው ምዕራፍ በአዋጁ የተመለከቱትን የአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎችን ከመከተል አንጻር ማለትም የአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ አጀማመር፣ ጉዳዩን ስለመስማት፣ የአስተዳደር ውሳኔ ይዘት፣ በተገቢው ጊዜ ከመወሰን አንጻር እና በአስተዳደር ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ ጋር በተያያዘ ያለው አፈጻጸም ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍም በዳግም ክትትሉ ከተለዩ ግኝቶች በመነሳት መደምደሚያ እና ምክረ ሀሳብ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# መመሪያን ከማውጣት እና ከማስመዝገብ ሂደት አንፃር

## 2.1 መመሪያን ስለማውጣት (አንቀጽ4)

በቀድሞ ክትትል ተቋሙ በሕግ በተሰጠው ውክልና ሥልጣን መሠረት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋሉን ተመልክተናል፡፡ በቀድሞ ክትትል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያላወጣው መመሪያ ስለመኖሩ ያልተመለከተ በመሆኑ በዚህ ዳግም ክትትልም በዚህ ረገድ የሚነሳ ግኝት የለም፡፡

## 2.2 መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ (አንቀጽ 5)

በአዋጁ አንቀጽ አምስት መሠረት አስገዳጅ መመሪያዎች በሶስት ወር መውጣት እንዳለባቸው የሚደነግግ ሲሆን በቀድሞ ክትትል ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአስገዳጅ ሁኔታ መመሪያ እንዲያወጣ የሚያዝ አዋጅ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያለውን

አፈጻጸም መገምገም አልተቻለም ነበር። በዚህ የዳግም ክትትልም አዲስ ግኝት አይኖርም። በሌላ በኩል አስገዳጅ ባልሆነ ሁኔታ መመሪያ እንዲያወጣ በተሰጠው ስልጣን መሠረት መመሪያዎችን አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋሉን ተመልክቶ የነበረ ሲሆን በዚህ የዳግም ክትትል አስገዳጅ ባልሆነ ሁኔታ እንዲያወጣ በሚጠበቅበት ጉዳዮች ላይ ረቂቅ መመሪያዎችን የማዘጋጀት ሂደት ላይ ይገኛል።

በአጠቃላይ ተቋሙ በቀድሞ ክትትልም ሆነ አሁን በዳግም ክትትል በእናት ሕጉ መመሪያ እንዲያወጣ በአስገዳጅ ሁኔታ የተቀመጠ ድንጋጌ ባይኖርም ለሥራው አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መመሪያዎችን በማውጣት ሥራ ላይ ማዋሉ አሁንም መመሪያዎችን ለማውጣት በረቂቅ ዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ በጥንካሬ ታይቷል።

## 2.3 የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ- ሥርዓት

የቀድሞ ክትትል ሪፖርት ከተደረገ በኃላ የሚኒስቴር መስሪ ቤቱ ያጸቀደው መመሪያ የለም፡ ይሁን እንጂ እየተዘጋጁ ያሉ ረቀቅ መመሪያዎችን ባሉበት ወይም በደረሱበት ደረጃ በአዋጁ የተማለከቱ ሥነ-ሥርዓቶችን ከመከተል አንጻር አፈጻጸማቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ሀ. መዝገብ ከማደራጀት አንጻር (አንቀጽ 7)

በቀድሞ ክትትል መሰረት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መዝገብ በማደራጀት ረገድ የተሰራ ስራ አልነበረም። በዚህ የዳግም ክትትል በረቂቅ ደረጃ ላይ ያሉ የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ፣ አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ እንዲሁም የጤና አጠባበቅ ቆሻሻ አያያዝ መመሪያን በተመለከተ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መዝገብ እንደሚያደራጁ ከመግለጽ ባለፈ በተግባር የተዘጋጀ መዝገብ አልተገኘም። መዝገብ ማደራጀት መመሪያው ከመነሻው ጀምሮ ያለበትን እና እየደረሰበት ያለበትን ደረጃ እየሰነዱ ለማስቀመጥ የሚረዳ በመሆኑ ረቀቂቅ መመሪያው ሲዘጋጅ ከመነሻውም አብሮ ሊዘጋጅ ይገባል። በመሆኑም ሚኒስቴሩ በቀድሞ ክትትል የተሰጠውን ምክረ-ሃሳብ ተግባራዊ አለማድረጉን የሚያሳይ ነው።

### ለ. ማስታወቂያ ከማውጣት አንጻር (አንቀጽ 8)

በቀድሞ ክትትል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ላወጣው አንድ መመሪያ ማስታወቂያ አልወጣም ነበር። በዚህ ዳግም ክትትል ግኝት መሰረት ታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ/ም በፌስ-ቡክ እና በድረ-ገጹ ላይ በወጣዉ ማስታወቂያ ከላይ በተገለጹት ሶስት ረቂቅ መመሪያዎች ላይ

'ማስፈንጠሪያውን በመከተል በመመሪያዎቹ ላይ አስተያየት ያላቸው ሰዎች እስከ ጥር 20 ቀን 2015 ዓ/ም ድረስ አስተያየታችውን  በኢሚይል አድረሻ መላክ የሚቻል ስለመሆኑ መውጣቱ ታይቷል፡፡ እንዲሁም የጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ ኃላፊና ሰራተኞች በቃለ-መጠይቅ የተገኘው መረጃ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለ ረቂቅ መመሪያዎቹ በፌስቡክና በድረ-ገጹ ማስታወቂያ በማውጣት መጫኑ መልካም ጅምር ቢሆንም ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ማስታወቂያው አለማውጣቱ በክፍተት ታይቷል፡፡

## ሐ. ለአስተያየት ለባለድርሻ ከመላክ አንጻር (አንቀጽ 9)

በቀድሞ ክትትል መሰረት ረቂቅ መመሪያው ለሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማለትም የጤና ሙያ ማህበራት ረቂቅ መመሪያው ተልኮ በአካል መጥተው ስለመወያየታቸው እንጂ አስተያየታቸውን በጽሑፍ እንዲልኩ አለመደረጉ ታይቶ ነበር፡፡ በተደረገው ዳግም ክትትል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሂደት ላይ ያሉ ረቂቅ መመሪያዎች ለባለድርሻ አካላት የጽሁፍ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የተላኩ ስለመሆኑ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህም ባለፈው የተሰጠው ምክረ ሀሳብ ተግባራዊ አለመደረጉን የሚያሳይ ነው፡፡

## መ. የውይይት መድረክ ከማዘጋጀት አንጻር (አንቀጽ10)

በቀድሞ ክትትል ሪፖርት መሰረት ከባለድርሻ አካላት ውጭ ማንኛውም ሰው ሊሳተፍ የሚችልበት የተዘጋጀ የውይይት መድረክ አልነበረም፡፡ በዚህ የዳግም ክትትል በሜዲካል አገልግሎት ሥራ አስፈፃሚ የሥራ ሒደት በተዘጋጀው "የህክምና ኦክስጅን ማምረቻ ፕላንት አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ" ላይ ለማንኛውም ሰው ሳይሆን ከሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላትና ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድክ ተዘጋጅቶ እንደነበር መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም በቀድሞ ክትትል የተፈፀመው ክፍተት አሁንም በዳግም ክትትል አለመታረሙን ለመመልከት ተችሏል፡፡

## ሠ. የመመሪያ ይዘት ከማሟላት አንጻር (አንቀጽ 15)

በቀድሞው ክትትል መሰረት የወጣው አንድ መመሪያ በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ የተዘጋጀ ነበር። በአዋጁ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ባሟላ ሁኔታ የተዘጋጀ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህ ዳግም ክትትል በረቂቅ ደረጃ ላይ የሚገኙ መመሪያዎች የመመሪያው ተራ ቁጥር፣ መመሪያው እንዲወጣ የሥልጣን ምንጭ የሆነውን ሕግ፣ የመመሪያውን አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ የተፈፃሚነት ወሰን፣ ዋና ዋና ድንጋጌዎች፣ የማሻሻያ፣ መሻሪያ፣ መሸጋገሪያ፣ ማቆያ ድንጋጌ ካለ ይህንኑ የሚመለከት ድንጋጌዎች የያዙ በመሆኑ በዚህ ረገድ የይዘት ችግር የሌለባቸው ስለመሆኑ ታይቷል። በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከማዘጋጀት አንጻር ግን መመሪያዎች በረቂቅ ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆኑ መገምገም አልተቻለም።

## ረ. መመሪያን ለፍትህ ሚኒስቴር አስተያየት ከመላክ አንጻር (አንቀጽ 12)

የተዘጋጁ ረቂቅ መመሪያዎች ለፍትሕ ሚኒስቴር የሚለኩበት ደረጃ ላይ አልደረሱም።

## ሰ. መመሪያን ከማስመዝገብ አንጻር (አንቀጽ 13)

የተዘጋጁ ረቂቅ መመሪያዎች ለፍትሕ ሚኒስቴር ተልከው የሚሚዘገቡበት ደረጃ ላይ አልደረሱም።

## ሸ. መመሪያዎችን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር (አንቀጽ 17)

በቀድሞ ክትትል መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በድረ-ገጽ መመሪያዎቹን አለመጫኑ በክፍተት ታይቶ ነበር። በዚህ ዳግም ክትትል የሕግ ክፍሉ ለመስሪያ ቤቱ ሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን መሪ ሥራ አስፈፃሚ ድረ-ገጽ ሁሉንም የጸደቁ የተቋሙ መመሪያዎች በተደራጀ መልኩ እንዲጫኑ መመሪያዎቹን በሲዲ አድርጎ መላኩ የተገለጸ ቢሆንም እስከ አሁን አለመጫኑ ታይቷል። ይህም ቀድሞ የተሰጠው ምክረ ሀሳብ ተግባራዊ አለመደረጉን የሚያሳይ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት ዳሰሳ

## 3.1 አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመስጠት አንፃር የታዩ ግኝቶች

የአስተዳደር ውሳኔ ማለት መመሪያ ማውጣትን ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 2/2/ የተገለፀ ሲሆን፤ በአዋጁ አንቀጽ 20 ደግሞ የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ ጉዳዩ በሚመለከተዉ ሰዉ ወይም በወኪሉ ወይም በሚመለከተዉ የአስተዳደር ተቋም አነሳሽነት ሊጀመር እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ረገድ ቀድሞ በተደረገው ክትትል መሰረት በአዋጁ ላይ የተቀመጡትን መርሆዎች እንዲከተል የተሰጠውን ምክረ ሀሳብ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ በተመለከተ የሚከተሉት ዝርዝር ግኝቶች ቀርበዋል፡፡

## ሀ. የአስተዳደራዊ ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ

በቀድሞ ክትትል መሠረት የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ በሚመለከተዉ ሰዉ ወይም በወኪሉ በአብዛኛው በጽሑፍ አንዳንዴ በቃል የሚቀርቡ መኖራቸው ታይቶ ነበር፡፡ መተማመኛ ከመስጠት አንጻር በመዝገብ ቤት በኩል የማረጋገጫ ጽሑፍ የሚሰጥ ቢሆንም ከአቤቱታው ጋር ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ዝርዝር የሚያሳይ ማረጋገጫ የማይሰጥ መሆኑን ታይቶ ነበር፡፡ እንዲሁም አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጥልኝ ማቅረቢያ ቅጽ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተዘጋጅቷል፡ ከዚህ አንጻር በዳግም ክትትል የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ በአዋጁ አንቀጽ 20፣ 21፣ እና 22 መሠረት ጉዳዩ በሚመለከተዉ ሰዉ ወይም በወኪሉ ሊቀርብ መቻሉና አቀራረቡም በአካል ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚቀርብ መሆኑ ታይቷል፡፡ ለአብነትም

1. የጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ በኢሜል አቤቱታ የሚቀበል ስለመሆኑ፣

2. የሜዲካል አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ፣

3. የተቋማዊ ለውጥ ሥራ አስፈፃሚ እና የቅሬታና አቤቱታ ቡድን ፣

4. የፌዴራል የጤና ባለሙያዎች ሥነ-ምግባር ኮሚቴ

በጽሑፍ ሆኖ በአካል የሚቀበሉ ስለመሆኑ ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ስለመቀበላቸው ማስረጃ አይሰጡም፡፡ ይህም ማረጋገጫ ከመስጠት አንጻር ያለው ክፍተት እንዲስተካከል የተሰጠው ምክረ ሀሳብ ተግባራዊ አለመደረጉ ታይቷል፡፡

## ለ. ጉዳይን ከመስማት አንጻር (አንቀፅ 28)

በቀድሞ ክትትል ወደ ተቋሙ የተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚቀርቡ አቤቱታዎች እና ቅሬታዎች በአብዛኛው በሰነድ ማስረጃ የሚደገፉ እና የሚረጋገጡ ቢሆንም የሰው ማስረጃም ጭምር አስቅርቦ የመስማት አሰራር መኖር (ለምሳሌ የጤና ሙያተኞች ሥነ ምግባር ክትትልና አጣሪ ኮሚቴ)፤ ባለጉዳዮች እራሳቸው ቀርበው የሚሰጡትን ማብራሪያ የማዳመጥ እና የሰነድ ማስረጃዎችን በአግባቡ የመቀበል እና የመመርመር አስራር መኖሩን ታይቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የጤና ሙያተኞች ሥነ-ምግባር ክትትልና አጣሪ ኮሚቴ ጉዳዩን ከተከሰሰው ሰው ጋር ፊት ለፊት ስለማያከራክሩ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብትን የሚያጣብብ መሆኑ ተመላክቶ ነበር፡፡ በዳግም ክትትል መሰረት ጉዳይን ከመስማት አንጻር የጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ በኢሜይል የተላከለትን አስተዳራዊ ውሳኔ ይሰጥልኝ ጥያቄና ተያይዞ የቀረበውን ማስረጃ ይመረምራል፤ ያልተሟላ ማስረጃ ካለ ተገልጋዩ እንዲያሟላ በማድረግ የሚመረምር መሆኑን፣ የሜዲካል አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ፣ በሐኪሞች ቦርድ ውሳኔ ለከፍተኛ ሕክምና ወደ ውጪ ሀገር ለሚሄዱ ሕሙማን አስታማሚዎችና ንቅለ ተከላ ለሚያካሂዱ፣ የውጪ ሀገር ዜጎች አስከሬን ምርመራ ውጤት ጋር በተያያዘና የሕክምና ማስረጃዎች አውተንትኬት (እንዲረጋገጥ) እንዲደረግላቸው ለሚጠይቁ ተገልጋዮች በሐኪሞች ቦርድ የሚፈርሙ የሐኪሞችን የፊርማ ናሙና አስቀድሞ በመውሰድና በማገናዘብ በተጨማሪ በስልክና በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴዎች የሚመለከታቸውን የሆስፒታል ባለሙያዎችና ሰራተኞች በመጠየቅ መረጃና ማስረጃ የመውሰድ ዘዴን የሚጠቀሙ መሆኑን፣ የተቋማዊ ለውጥ ሥራ አስፈፃሚ እና የቅሬታና አቤቱታ ቡድን እና የፌዴራል የጤና ባለሙያዎች ሥነ-ምግባር ኮሚቴ የሚቀርቡ አቤቱታዎች እና ቅሬታዎች በአብዛኛው በሰውና በሰነድ ማስረጃ የሚደገፉበት ባለጉዳዮች የሚደመጡበትና በመጨረሻም ፍሬ ነገር እና ማስረጃ በሚገባ የሚመርመር ስለመሆኑ ታይቷል፡፡ በመጀመሪያዉ የክትትል ሪፖርት ተመላክቶ የነበረው የጤና ሙያተኞች ሥነ-ምግባር ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ባለጉዳዮች ባሉበት የማከራከር እና ባለጉዳዮች የቀረበባቸውን መረጃ እንዲሰሙ እና እንዲጠይቁ በማድረግ አሰራሩ ማሻሻያ የተደረገበት መሆኑ ውጤቱ ያመለክታል፡፡

## ሐ. በቅሬታ ላይ ውሳኔውን ለተገልጋይ ከመስጠት አንጻር (አንቀጽ 46)

በቀድሞ ክትትል ግኝት መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቅሬታ አቤቱታው መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠቱ ጥሩ አስራር መሆኑን ታይቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ውሳኔዎቹ ለቅሬታ አቅራቢው የሚሰጥብተን ጊዜ በተመለከተ ወዲያውኑ ስለመሆን አለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል ማረጋገጫ አላገኘንም፡፡ በቃል የሚቀርቡ አቤቱታወች/ቅሬታዎች በቃል እንጅ በጹህፍ የማይሰጡባችው የስራ ክፍሎች መኖራቸው በክፍተት ታይቶ ነበር፡፡

የተሰጠውን ምክረ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በቅሬታ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ወዲያውኑ በአዋጁ አንቀጽ 47 መሠረት ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መሰጠቱ እንዲሁም በቃል የሚሰጡ ውሳኔዎች አለመኖራቸውም ዳግም ክትትሉ አመላክቷል፡፡

## መ የአስተዳደር ውሳኔ ይዘት አንጻር (አንቀጽ 40)

በቀድሞ ክትትል መሰረት የውሳኔ ቀንና ቁጥር፣ የተቋሙን ስም፣ አመልካችን፤ በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፤ አከራካሪ ፍሬ ነገር፤ የማስረጃዎች ትንተና፤ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንታኔ እና ውሳኔ የያዘ ሆኖ ተመልክተን ነበር፡፡ በዳግም ክትትል በአዋጁ አንቀጽ 40 መሠረት የውሳኔ ቀንና ቁጥር፣ የተቋሙን ስም፣ አመልካችን፤ በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፤ እንደ አስፈላጊነቱ አከራካሪ ፍሬ ነገር፤ የማስረጃዎች ትንተና፤ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንታኔ እና ውሳኔ የያዘ ሆኖ ተመልክተናል፡፡ ይህም ከውሳኔ ይዘት አንጻር ያለው መልካም አሰራር ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

## 3.2 ቅሬታን በይግባኝ ከማየት አንፃር

## ሀ. ቅሬታን የማቅረብ መብት ከማክበር አንፃር (አንቀጽ 43)

በቀድሞ ክትትል ማንኛውም ሰዉ በተላለፈበት የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለአስተዳደር ተቋሙ ቅሬታ የማቅረብ ሙብት ተጠብቆ ቅሬታውን የሚያቀርብበት አካል ቢኖርም ቅሬታ ሰሚአካል መኖሩን ለተገልጋዮች ይፋ አልተደረገም ነበር ፡፡ በዳግም ክትትል በአዋጁ አንቀጽ 43 እና 44 መሠረት ተቋሙ ማንኛውም ሰዉ በተላለፈበት የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለአስተዳደር ተቋሙቅሬታ የማቅረብ ሙብቱን ለማክበር፤ ልዩ የቴክኒክ ሙያን የሚጠይቁ እንደ ጉዳዩ ዓይነት እና ባሕሪ ቅሬታ ማስተናገጃ ያቋቋመ ሲሆን፤

1ኛ. ከሕክምና ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚሚምሚውን አካል በቀድሞ ክትትል ጊዜ የነበረውን አደረጃጀት በማሻሻል እንዲሁም ተገልጋዮች ጉዳያቸው

በምክትል ሚኒስትሩ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥ የነበረውን በማሻሻል 12 አባላት ያሉት “የፌዴራል ጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ” ተጠሪነቱ ለምክትል ሚኒስትሩ ሆኖ ምክትል ሚኒስትሩ በሚሰጠው ውሳኔ ያልረካ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ እንዲችል ተደርጓል። አደረጃጀቱም አስፈላጊው ድጋፍ በጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሥራ ሂደት እንዲደረግለት ተደርጓል።

2ኛ. “የቅሬታና አቤቱታ ቡድን” በአዲሱ የተቋሙ አደረጃጀት በተቋማዊ ለውጥ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሥራ ሂደት የሚገኝ ሦስት አባላት ያሉት እንዲሆን ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡ በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች እና በጤና ጥበቃ ስር ከሚገኙ ሆስፒታሎች በተጨማሪ በክልል ማስተዳድር ስር ከሚገኙ ሆስፒታሎች የሚቀርቡ ጉዳዮችን መመልከቱ የጤና ባለሙያዎች በሙያ ብቃት ማዳደል በታካሚዎች ላይ በሚፈጸሙ ስህተት ለሚደርስ ጉዳት ከጊዜ፤ ከወጪ፤ ከተደራሽነት...ወዘተ አንፃር በየሆስፒታሎቹ ቅሬታ ማስተናገጃ አካል አለመቋቋሙ ከሚቀርቡ ጉዳዮች ብዛት አንፃር ጉዳዮች በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ በሚታየታቸው የውሳኔዎች ማዘግየት በክፍተት ተመልክተነዋል፡፡ እንዲሁም የቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል ለተገልጋዮች በድረ-ገጽም ሆነ በተቋሙ ግቢ በማስታወቂያ በመግለፅ ይፋ እንዲደረግ ተሰጥቶ የነበረው ምክረ ሀሳብ ተግባራዊ አለመደረጉ በክፍተትነት ሊወሰድ ችሏል፡፡

## ለ. ቅሬታውን ከመመርመርና ከመወሰን አንጻር (አንቀጽ 46)

በቀድሞ ክትትል በልዩ ጉዳይ የተቋቋመው የጤና ሙያተኞች ሥነ ምግባር ክትትልና አጣሪ ኮሚቴ የስራ ክፍል የቀረበላቸውን ቅሬታ በሚገባ መመርመር እና የዉሳኔ ሀሳብ ለአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ ለወከለዉ የሥራ ኃላፊ የሚያቀርቡበትን ጥሩ አስራር ተመልክተን ነበር፤ በአጠቃላይም የቀረበን ቅሬታ በሚገባ መመርመር እና የዉሳኔ ሀሳብ ለአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ከመስጠት አንጻር ያየነው ክፍተት አልነበረም፡፡

በዳግም ክትትል በአዋጁ አንቀጽ 46 መሠረት የአስተዳደር ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ቅሬታውን በሚገባ መመርመር እና የዉሳኔ ሀሳብ ለአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ማለትም ለምክትል ሚኒስትር/ሯ የማቅረብ አሰራር መቀጠሉ ታይቷል፡፡ እንዲሁም ከሕክምና ስህተት ውጪ ያሉ የውጪ ተገልጋዮችን ቅሬታ የሚመለከት 'የቅሬታና አቤቱታ ቡድን' በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለኃላፊ ያቀርባል፡፡ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ የወከለዉ የሥራ ኃላፊ በቅሬታ ማስተናገጃ አካል የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ የተቋሙ የመጨረሻ ውሳኔ በማድረግ ረገድ እየተሰራ ያለውን በጥንካሬ ተሰወስዷል፡፡

## ሐ. በቀረበ ቅሬታ ላይ ውሳኔውን ለተገልጋይ ስለማሳወቅ

በቀድሞ ክትትል በጹህፍ የቀረቡ ቅሬታዎችን በተወሰኑ የስራ ክፍሎች የአስተዳደር ተቋሙ በቅሬታ አቤቱታው መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠቱ ጥሩ አስራር መሆኑን አይተናል፡፡ ይሁን እንጂ ውሳኔዎቹ ለቅሬታ አቅራቢው የሚሰጥብትን ጊዜ በተመለከተ ወዲያውኑ ስለመሆን አለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል ማረጋገጫ አላገኘንም፡፡ በቃል የሚቀርቡ አቤቱታዎች/ቅሬታዎች በቃል እንጅ በጹህፍ የማይሰጡባቸው የስራ ክፍሎች መኖራቸው በክፍተት ታይቶ ነበር፡፡

በዳግም ክትትል ተቋሙ በአዋጁ አንቀጽ 46 መሠረት የሰጠውን ውሳኔ ወዲያዉኑ በአዋጁ አንቀጽ 47 መሰረት ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠቱ እና በቃል የሚሰጡ ውሳኔዎች መቅረታቸው ታይቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# ማጠቃለያ እና ምክረ ሀሳብ

## 4.1 ማጠቃለያ

የተቋሙ የበላይ አመራሮች ለአዋጁ አፈጻጸም ልዩ ትኩረት ሰጥተው የቅርብ አመራር በመስጠት እና ክትትል በማድረግ ለመካከለኛ አመራሮች በአዋጁ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ መደረጉ እና የአዋጅ አፈጻፀምም ሕግ ክፍሉ ረቂቅ መመሪያ በሚያዘጋጁ የሥራ ክፍሎች ጭምር ፎካል ፐርሰን ሆኖ እንዲከታተል መደረጉ በጥንካሬ ታይቷል፤

በተቋሙ በረቂቅ ዝግጅት ላይ ባሉት የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ፣ አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ፣ የጤና አጠባበቅ ቆሻሻ አያያዝ መመሪያ እንዲሁም የህክምና ኦክስጅን ማምረቻ ፕላንት አስተዳደር መመሪያዎች በተመለከተ መዝገብ አለመደራጀቱ፣ ማስታወቂያ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ አለመውጣቱ፣ ለባለድርሻ አካላት ለአስተያየት አለመላኩ እንዲሁም የህዝብ ውይይት የሚመለከታቸውን አካላት ብቻ በመጥራት ማካሄዱ ከአዋጁ አላማ እና መንፈስ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ በቀድሞ ክትትል እንዲሻሻል ምክረ ሀሳብ የተሰጠበት ቢሆንም ያልተሻሻለ መሆኑ ተመላክቷል። በሌላ በኩል ማስታወቂያ በተቋሙ ድረ-ገፅ ላይ መውጣቱ በዚህ ረገድ መሻሻል መኖሩ ያመላክታል።

በተመሳሳይ በፍትሕ ሚኒስቴር የተመዘገቡ ሁሉንም የተቋሙ እና የተጠሪ ተቋማት መመሪያዎች በተደራጀ መልኩ ለዚህ አላማ የተዘጋጀ ድረ-ገጽ በመፍጠር አለመጫኑ አሁንም በክፍተትነት ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የተዘጋጁት መመሪዎች እንዲኖራቸው የሚጠበቅ ይዘትን አሟልተው ማግኘታቸው የተሻሻለ አፈፃፀም ተደርጎ ተወስዷል፡፡ መመሪያዎችን ለፍትህ ሚኒስቴር ለአስተያየት መላክን እና ማስመዝገብን በተመለከተ እየተዘጋጁ ያሉት መመሪያዎች ለዚህ ግምገማ በሚሆን ደረጃ ላይ የማይገኙ ባለመሆኑ ተቋሙን አፈፃፀሙን ማካታተል አልተቻለም፡

ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ አንፃር የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ አቀራረብ በጽሑፍ ሆኖ በአካል፣ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊቀርብ መቻሉ፣ ጉዳይ በአግባቡ መሰማቱ፣ የአስተዳደር ውሳኔም ሆነ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ ይዘቱን የጠበቀ ውሳኔ ለተገልጋዩ መሰጠቱ በጥንካሬ ታይቷል፤

ማረጋገጫ ከመስጠት አንጻር አቤቱታ ሲቀርብለት አቤቱታውን በተረከበበት ጊዜ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑን መዝግቦ በቀሪው ላይ ፊርሞ የማረጋገጫ ጽሑፍ መስጠቱ በጥንካሬ ታይቷል፤ ይሁን እንጂ የማረጋገጫ ጽሑፉ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑንና ከአቤቱታው ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ዝርዝር የሚያሳይ አለመሆኑ፣ ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ቢያቋቁምም ማቋቋሙን ለተገልጋዮች ይፋ አለማድረጉ በቀድሞ ምክረ ሀሳብ መሰረት ሳይሻሻል የቀረ መሆኑ ግኝቱ ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በአዋጁ ዙርያ ተገቢውን ድጋፍ በፍትህ ሚኒስቴር በኩል የተሰጠ ቢሆንም መመሪያን በተገቢው መንገድ ከማውጣት አንጻር የተቋሙ አፈጻፀም ደካማ የሚባል ሲሆን በአንፃራዊ ተቋሙ አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የተሻለ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡

## 4.2. ምክረ ሀሳብ

- ተቋሙ በመመሪያ አወጣጥ፣ አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት የአዋጁን ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ እየፈፀመ ያለውን ጥንካሬ የበለጠ አጠናክሮ እንዲያስቀጥል፡
- የመመሪያ አወጣጥ ቅድመ ስርዓቶች በአዋጁ በግልፅ የተቀመጡ፣ የማያሻሙ እና ቀላል በመሆናቸው ተግባራዊ የሚሆኑበትን እና የህግ ክፍሉም ይህንኑ ለመከታተል የሚያስችል የውስጥ ስርዐት ቢዘረጋ፤
- በተቋሙ የወጡና በፍትሕ ሚኒስቴር የተመዘገቡ መመሪያዎች በተቋሙ ድረ-ገጽ ቢጫን፣
- ተቋሙ አቤቱታ ሲቀርብለት የማረጋገጫ ጽሑፉ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑንና ከአቤቱታው ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ዝርዝር የሚያሳይ የጽሁፍ መተማመኛ ለተገልጋዩ እንዲሰጥ ቢደረግ፤
- በተቋሙ የተቋቋመውን የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ስለማቋቋሙ በድረ-ገጹ እና በተቋሙ ግቢ ተገልጋዮች ሊያዩት በሚችሉት ቦታ በማስታወቂያ ቢገለጽ፤

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ ፡ በክትትሉ የተዳሰሱ ዋቢ ሕጎች

### ሀ. ሥልጣን ሰጪ ሕጉች

1. የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014
2. የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011
3. ሀገር አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤትና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 276/1994።

### ለ. ሌሎች ሕጎች

1. የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 529/2015
2. የኢትዮጵያ የምግብ እና የመድሐኒት ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 531/2015
3. የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገሌግልት ማ ቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 486/201
4. የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጄንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 191/2003
5. የማኅበራዊ ጤና መድኅን አዋጅ ቁጥር 690/2002
6. የማኅበራዊ ጤና መድኅን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 271/2005
7. የኢትዮጵያ የደም እና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 528/2015
8. የኤካ ኮተቤ ሆስፒታል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዯንብ ቁጥር 467/2012
9. የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች 376 2008 ደንብ ቁጥር 530/2015
10. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 200/2003
11. የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 535/2015
12. የመድኃኒት ፈንድን እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ 553/1994

13.የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 699/2006

14.የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የአዋጅ ቁጥር 661/2002

15.የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 167/2001

16.የምግብ የመጠጥና ፋርማሲቲዩካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 287/2005

17.የሕዝብ ጤና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 200/1992

## አባሪ ሁለት፡ መመሪያ ለማውጣት ስልጣን የሚሰጡ የአዋጅ ድንጋጌዎች ዝርዝር

1. የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አ19.4
2. የሕዝብ ጤና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 200/1992 አ/23/
   የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር
3. 661/2002 አንቀጽ /55/3/ 770 54/3/
4. የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 73 እና 661/02 አ3/2መ/ እና አ4/16/
5. የመድኃኒት ፈንድና የመድኃኒት አቅርቦት አጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 553/1994 (ቦርድ) 1263/2013
6. የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 167/2001 አንቀጽ 15

## አባሪ ሶስት፡ በክትትሉ የታዩ ሌሎች ሰነዶች

1. ጥር1/ 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ የጤና ሚኒስቴር አዲሱ መዋቅር ጥናት እና ምደባን ሚመለከት አጭር ማብራሪያ ገጽ ሶፍት ኮፒ፣

2. በቁጥር cdml/4951/1083 በ8/10/2015 ለመንግሥት ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎችና ለሌሎች ባለድርሻ ሆስፒታሎች በረቂቅ መመሪያ ላይ ውይይት ለማድረግ ጥሪ የተደረገበት 1 ገጽ ሶፍት ኮፒ፣

3. ነሐሴ 2015 ዓ/ም የተዘጋጀ የጤና ሚኒስቴር የሕግ አገልግሎት ሥራ አስፈፃሚ ረቂቅ የዜጎች የስምምነት ሠነድ 1 ገጽ ሶፍት ኮፒ፣

4. ከሕግ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ በቁጥር የሕግ/አ/ሰ/985/15 በ13/10/2015 ሁሉም የሥራ ክፍሎች አንድ አንድ የስልጠና ተሳታፊ እንዲልኩ የተፃፈ ደብዳቤ 1 ገጽ ሶፍት ኮፒ፣

5. ከሕግ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ በቁጥር የሕግ/አ/ሰ/34/16 በ30/ 1/2016 ዓ/ም ሁሉም የሥራ ክፍሎች የ206 ዓ/ም የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅትን ይመለከታል በሚል የተፃፈ ደብዳቤ 1 ገጽ ሶፍት ኮፒ፣


6. ከሚስትሯ ለጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ በቁጥር ጤጠ/6/44/153 በ18/5/15 የጤና ሙያተኞች ሥነ ምግባር ክትትልና አጣሪ ኮሚቴ አሰራርን በተመለከተ የተፃፈ ደብዳቤ 1 ገጽ ሶፍት ኮፒ፣


7. አዲስ የተዘጋጀ የዜጎች ቻርተር


8. ከሕግ ክፍል ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሺን መሪ ሥራ አስፈፃሚ በቁጥር የሕ/ጉ/ዳ/83/86 በ6/3/16 የተፃፈ ደብዳቤ 1 ገጽ ሶፍት ኮፒ፣


9. ጁን 2/2023የተፃፈ ደብዳቤ 1 ገጽ ሶፍት ኮፒ፣ በተቋሙ ድረ-ገጽ በመመሪያዎች ላይ አስተያየት መስጠት እንደሚቻል መገለፁን የሚገልጽ

## አባሪ አራት፡- የሚኒስቴሩ ተቋማዊ አደረጃጀት መግለጫ




ሚኒስትር
የሥርዓተ-ምግብ ማስተባበሪያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ
የፖሊሲና ስትራቴጂ ጥናትና ምርምር መሪ ሥራ አስፈጻሚ
የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ
መከላከል-ተኮር ሥርዓተ-ምግብ ዴስክ
የኤች አይ ቪ እና የአበላዘር በሽታ መከላከል ዴስክ
ምገባ-ሕክምና ዴስክ
የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሕክምና እና ክብካቤ ዴስክ
የዘርፍ ብዙ እና ሰቆጣ ቃል ኪዳን ማስተባበሪያ ዴስክ
የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ምላሽ ማስተባበሪያ ዴስክ


ሚኒስትር
የጤና አገልግሎት እና ፕሮግራም ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
የእናቶች፤ ሕጻናት እና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈጻሚ
የእናቶች ዴስክ
የሥነ-ተዋልዶ ጤና የቤተሰብ ዕቅድ እና የአፍላ ወጣቶች ጤና ዴስክ
የጨቅላ ሕጻናትና የሕጻናት ጤና ዴስክ
የክትባት አገልግሎት ዴስክ
የማህበረሰብ ተሳትፎ እና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ መሪ የሥራ አስፈጻሚ
የማህበረሰብ ተሳትፎ እና የጤና ኤክስቴሽን አገልግሎት ዴስክ
የሀይጅንና የአከባቢ ጤና አጠባበቅ ዴስክ
የጤና ጣቢያ አገልግሎት ዴስክ
የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ
የወባና ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዴስክ
የተቢ የሥጋ ዳዌና ሌሎች የሳንባ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዴስክ
ትኩረት የሚሹ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዴስክ
ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና የአእምዕሮ ጤና መከላከልና መቆጣጠር ዴስክ
የሜዲካል አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈጻሚ
የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሽያ ዴስክ
የስፔሻሊቲና ተሃዲሶ አግልግሎት ዴስክ
የድንገተኛ እና ጽኑ ሕሙማን አገልግሎት
የሕሙማን ቅብብሎሽ አገልግሎት ዴስክ


ሚኒስትር
የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ
የመሠረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ
የንብረት ሥራ አመራር ቡድን
የተሽካሪካሪ ስምሪትና ጥገና ቡድን
የሕንጻዎች አስተዳደር እና ጥገና አገልግሎት
ጠቅላላ አገልግሎት
የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ
የዕቅድና በጀት፣ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ቡድን
የፕሮጀክት አስተዳደር፣ አጋርነትና ሀብት ማፈላለግ ቡድን1
የፕሮጀክት አስተዳደር፣ አጋርነትና ሀብት ማፈላለግ ቡድን 2
ስታቲክስና መረጃ ቡድን
የፋይናንስ ሥራ አስፈጻሚ
የፋይናንስ ቡድን 1
የፋይናንስ ቡድን 2
የግዥ ሥራ አስፈጻሚ
የግዥ ቡድን
የውል አስተዳደርና ክትትል ቡድን
የተቋሚ ለውጥ ሥራ አስፈጻሚ
የአቤቱታ ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን
የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሥራ አስፈጻሚ
የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ቡድን
የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ትግባራ ሥራ አስፈጻሚ
የሰቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች አካቶ ትግበራ ቡድን
የማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ትግበራ ቡድን
የብቃት እና ሰው ሀብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ
የሰው ሀብት አስተዳደር ቡድን
የሰው ሀብት ብቃትና ልማት ቡድን
የሠራተኛ ማበረታቻና አገልግሎት ቡድን
የምግብ ዝግጅት አገልግሎት
የሪከርድና ማህደር ሥራ አመራር አገልግሎት

**አባሪ አምስት የሚኒስቴሩ ተጠሪ ተቋማት**

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት

የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣

የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት፣

የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲቲዩት፣

የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት፣

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት፣

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን፣

ቅዱስ ጴጥሮስ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣

አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት፤

የ ኤካ ኮተቤ አ ጠቃላ ይ ሆስ ፒ ታል፡ ፡

**አባሪ ስድስት፡ አዋጁ ከወጣ በኂላ የወጡ እና ያልተመዘገቡ ለናሙና የተጠቀምንባቸው መመሪያወች ዝርዝር፤ (ጅምር በመረቂቅ ላይ ያሉ)**

በቀዳሚ ምርመራ አዋጁ ከወጣ በኃላ የወጣ አንድ አዲስ መመሪያ መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡ ያልተመዘገበ የለም

አሁን የተዘጋጁት ረቂቅ መመሪያዎች በሂደት ላይ ስለሆኑ ለምዝገባ አልደረሱም

1) የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ -

2) አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ

3) Waste Management Directive No.

4) የህክምና ኦክስጅን ማምረቻ ፕላንት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር

**አባሪ ሰባት፡ ለናሙና የተመለከተናቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ዝርዝር**

አስፈላጊውን ማስረጃ አቅርበውና ፈቃድ ለመውሰድ ፈተና አልፈው ውጤት በኢሚይል የተገለፀላቸው

የጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ

1. ዳንኤል አበበ ጉርሙ በ7/1/16 አመለከተ በ9/1/16 ውሳኔ ደረሰው

2. ለይላ ጅብሪል በ5/1/16 አመለከተች በ9/1/16 ውሳኔ ደረሳት

3. ኢማን ረድ በ6/1/16 አመለከተች በ9/1/16 ውሳኔ ደረሳት

4. ዮሃንስ አዴሎ በ6/1/16 አመለከተ በ9/1/16 ውሳኔ ደረሰው

5. አብዲ

6. ሴና አበበ

7. ሪሀን መላኩ በ8/1/16 አመለከተች በ10/1/16 ውሳኔ ደረሳት

8. ሰላም ወንድአፍራሽ በ9/1/16 አመለከተች በ10/1/16 ውሳኔ ደረሳት

9. ሀበክ ካሳዬ በ10/1/16 አመለከተ በ10/1/16 ውሰኔ ደረሰው

10. ማይክል አልዩ በ10/1/16 አመለከተ በ10/1/16 ውሳኔ ደረሰው

11. ዳንኤል አበበ በ7/1/16 አመለከተ በ9/1/16 ውሳኔ ደረሰው

ፈቃድ ለመውሰድ አስፈላጊውን ማስረጃ ባለሟሟላታቸው እንዲያሟሉ በኢሚየል አድራሻቸው የተገለፀላቸው

12. ፍሬድሪካ አልዛቤት ኮሊንስ (ኒዘርላንድ ሴት)

13. ለማሪያ ታቦዳ ታቡንካ (ስፔን ወንድ)

14. ጁዲዝ አግወር አግወር (ኡጋንዳ ሴት)

15. ፓሩል ካታያር ራምሻንካር (ኢንዲያ ሴት )

16. ዳንኤል ኪዳኔ ተክሌ (ኤርትራ ወንድ)

17. ሶክ ሁይ ጎህ (አውስትራሊያ ሴት)

18. ኤልሳ ነጽረአብ እቁበሥላሴ (ኤርትራ ሴት)

በፌዴራል ጤና ባለ-ሙያዎች ሥነ-ምግባር ኮሚቴ የታዩ

19. በአመልካች አ/አ/ፖሊስ ከ/ በተጠሪ የቅ/ጴጥሮስ ሆስፒታል በቁጥር በየሕ/ቅ/መ/ቁ/156 በ8/10/2014 ዓ/ም የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ እና ውሳኔ

20. በከሳሽ ወ/ሮ ታደለች ሀብቴ በተከሳሽ ወዲዩ ክልኒክ በቁጥር በየሕ/ቅ/መ/ቁ/176 በ18/8/2015 ዓ/ም የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ እና ውሳኔ

21. በአመልካች የካ ክ/ከ/ ፖሊስ በተጠሪ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል በቁጥር በየሕ/ቅ/መ/ቁ/103 በ21/3/2015 ዓ/ም የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ እና ውሳኔ

**አባሪ ስምንት ጉዳያቸው ሳይታይ የዘገየባው ቅሬታ አቅራቢዎች**

- ህፃን ኢዩኤል ቅ/ጳውሎስ ሆስፒታል ካርድ ባለመገኘቱ 2011 ዓ/ም
- ሀያት ከሊፋ ከጂማ ዩንቨርስቲ የሞት ምስክር ወረቀት ጥቅ 2010
- አዕምሮ ወሊ ቅ/ጳውሉስሆ/ል ካርድ 2008 ዓ/ም
- አያልነሽ ምኒልክ ሆ/ል 2010 ዓ/ም የአስከሬን ምርመራ ውጤት
- ፈቃዱ ገላው 2009 ዓ/ም scope of practice እና ባለሙያ ባለመቅረቡ

ቅሬታቸው ሊታይ አልቻለም፡፡

**አባሪ ዘጠኝ፡ ቃለ- መጥይቅ ያደረግንላቸው እና መረጃ የሰጡን የሥራ ኃላፊዎች ዝርዝር**

1. ክብርት ዶክተር መሠረት ዘላለም የሴቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ኃላፊ
2. ቤተል ገመዳ የሥነ ተዋልዶ ጤና አማካሪ
3. አቶ ሽለመ የእናቶችና ጤና ከፍተኛ ባለሙያ
4. አቶ ትቤሶ ሎዳሞ የሕግ አገልግሎት መሪ ሥ/አስፈፃሚ ኃላፊ
5. አቶ ተመስገን የሕግ ባለሙያ
6. አቶ ብርሃን በቀለ የሕግ ባለሙያ
7. እንዳልካቸው ፀዳል የጤናና ጤና ነክ ተቋማት እና ባለሙያዎች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ ኃላፊ
8. የዚሁ ሥራ ክፍል አማካሪ አቶ መሳፍንት አበጀ
9. አቶ ቢኒያም ከማል የሜዲካል አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ የሆስፒታልና ዳግኖስቲክ ሥራ አስፈፃሚ ኃላፊ
10. አቶ ገረመው ኡጋ የተቋማዊ ለውጥ ሥራ አስፈፃሚ ኃላፊ እና
11. አቶ እንቁ ባህሬ የቅሬታና አቤቱታ ቡድን መሪ
12. ወ/ሮ ቤተልሔም የሕግ ባለሙያና የፌዴራል የጤና ባለሙያዎች ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ፀሐፊ

**አባሪ አስር፡- የቃለ- መጠይቅ ጥያቄዎች**

የመንግስት አስተዳደር ተቋማት የፌዴራል የአስተዳደር ሥነስርዓት ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አተገባበርን ለመፈተሽ ለሚደረገው ጥናት ከተቋማት ባለሙያዎችና ኃላፊዎች መረጃ ለመሰብሰብ ይረዳ ዘንድ የተዘጋጀ ቃለመጠይቅ

**1.የአዋጁ ግንዛቤ አንፃር የተዘጋጁ ጥያቄዎች**

- በተቋማችሁ የፌዴራል አስተዳደር ሥነስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር ተደርጎ ያውቃል? መልስዎ አዎ ከሆነ ማሳያዎች ያስፈልጋሉ

- የፌዴራል የአስተዳደር ሥነስርዓት አዋጅ አፈጻፀም የሚከታተል ወይም የሚያስተባብር አካል በተቋሙ ተዘጋጅቷል ወይ?

## 2. ከመመሪያ አወጣጥ ጋር በተያያዙ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

### 2.1 የመመሪያ ማውጫ ጊዜ

- በአ/ሥ/ሥ/ ሕግ አዋጅ አስገዳጅ የመመሪያ ማውጫ የሦስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ መውጣት ሲገባው ያልወጣ መመሪያ አለ?

### 2.2 ነባር መመሪያ ከማስመዝገብ አንጻር

- የአስተዳደር ሥነስርዓት ሕግ ከመውጣቱ በፊት በተቋሙ የወጡ ምን ያህል ነባር መመሪያዎች አሉ እነዚህ መመሪያዎች ለፍ/ሚ/ ተልከው ተመዝግበዋል ወይ? ያልተመዘገቡ ካሉ በዝርዝር ቢገልጹ የአ.ሥ ሥ. ሕግቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 16(4) የወጣ አዲስ መመሪያ ካለ ብቻ የሚመለስ

### 2.3 አዲስ መመሪያ የማውጣት ሂደት

- ተቋማችሁ የአሰተዳደር ሥነሥርዓት ሕጉ ከወጣ በኂላ (መጋቢት 2012 ዓ/ም) አዲስ መመሪያ አውጥቷል ወይ? አዎ ከሆነ በዝርዝር ቢገልጹ
- ተቋማችሁ የመመሪያ አወጣጥ መዝገብ አደራጅቷል ወይ? የአ.ሥ ሥ. ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 6(1)
- ተቋማችሁ የአሰተዳደር ሥነሥርዓት ሕጉ ከወጣ በኂላ (መጋቢት 2012 ዓ/ም) አዲስ የሚወጣ ረቂቅ መመሪያን በተመለከተ ለህዝብ ተደራሽ በሆነ ጋዜጣ ወይም መገናኛ ብዙሃን ወይም በተቋማችሁ ድረ-ገጽ አስተያት ለመሰብሰብ የማስታወቂያ ጥሪ ተደርጓል ወይ ካላደረገ ለምን
- በተቋማችሁ አዲስ የተዘጋጀ ረቂቅ መመሪያ ካለ ለባለድርሻ አካላትና ለሚመለከታቸው አስተዳደር ተቋማት አስተያየት እንዲሰጡበት ተልኮ ያውቃል? ማሳያዎች ማቅረብ ያስፈልጋል የአ.ሥ ሥ. ሕግቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 9(1)
- አዲስ በተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ አስተያየት ለመሰብሰብ ተቋማችሁ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ያውቃል? ካላደረገ ለምን? የአ.ሥ ሥ. ሕግቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 10
- በረቂቅ መመሪያ ላይ የተሰጡትን አስተያየት መቀበል እና ማካተት በተመለከተ ተቋማችሁ ያለው አፈጻጸም ምን ይመስላል? የአ.ሥ ሥ. ሕግቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 12(2)

- አዲስ በሚወጣ ረቂቅ መመሪያ ላይ ተቋማችሁ የማብራሪያ ጽሁፍ ያዘጋጃል ወይ? የአ.ሥ ሥ. ሕግቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 14

**2.4 መመሪያን ከማስመዝገብ አንጻር**

- በተቋማችሁ የወጡ አዲስ ረቂቅ መመሪያ ከነማብራሪያው ለፍትሕ ሚኒስትር በመላክ እንዲመዘገብ ተደርጓል ወይ?

3. መመሪያተደራሽ ከማድረግ አንጻር

- ተቋማችሁ የጸደቀውን መመሪያ አሳትሞ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 17(2)
- የጸደቁ መመሪያዎች በሙሉ በተቋሙ ድረ ገጽ ይጫናል ወይ?
- በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቅጂከማዘጋጀት አንፃር

**3. ከአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች**

- በተቋማችሁ ለተገልጋዮች የሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች አይነት በዝረዝር ቢገልጹልን
- ተቋማችሁ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ቅጽ አዘጋጅቷል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 21(3)
- ተቋማችሁ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ለማስተናገድ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል አቋቁሟል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 44
- የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጠው ጥያቄ ላቀረበ ሰው ተቋማችሁ አቤቱታ መቅረቡን በተመለከተ ለአቤቱታ አቅራቢው ማረጋገጫ የሚሰጥበት አሰራርዘርግቷል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግአዋጅቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 22
- በተቋማችሁ አንድ የአስተዳደር ውሳኔ ለመስጠት የሚፈጀው ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የሚገልጽ አሰራር አለ ወይ? ተቋሙ ካስቀመጠው የዜጎች ቻርተር አንጻር በመነሳትጥያቄ መጠየቅ?
- በተቋማችሁ የሚሰጥ የአስተዳደር ጉዳይ ውሰኔ የመሰማት ሂደትን ያካትታል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 36

እነዚህም

- ምስክርነት የመስጠት፤
- ምስክሮችን እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማቅረብ እና የማሰማት፤
- ለተቋሙ የቀረቡ ማስረጃዎችን የመስማትና የመመርመር እንዲከበሩ ይደረጋሉ ወይ?

የአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ይዘት እና አኳኋን በተመለከተ በተቋማችሁ የአስ/ሥ/ሥ/ አዋጁ ባስቀመጠው ሥርዓት መሠረት የጠከተለ ነው መልስዎ አዎ ከሆነ ማሳያዎች ቢጠቅሱ

4. የአስተዳደር ሥ/ሥ/ አዋጁ ከወጣ በኋላ ከሰርኩላር ፣ ማንዋል፣ ወይመም ሌላ ስያሜ ያላቸው በዜጎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል ሰነዶች አሉ መልስዎ አዎ ከሆነ ማሳያዎች ይቅረቡ

**አባሪ 10፡- በባለስልጣኑ የተዘጋጁ ቅፃ ቅጾች**

ቅጽ አንድ አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥያቄ ማቅረቢያ

ቅጽ ሁለት አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥያቄ መልስ መስጫ

ቅጽ ሦስት በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥያቄ ላይ ቅሬታ ማቅረቢያ

ቅጽ አራት በአስተዳደራዊ ውሳኔ ቅረታ ላይ መልስ መስጫ

**Ministry of Health,Ethiopia**
2 Jan at 5:24 pm ·

ማስታወቂያ

___________

ጤና ሚኒስቴር የጤናና ጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥርን ለማጠናከር Health Care Waste Management Directive፣ የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ (Health Institution Service Promotion) እና የጤናና ጤና ነክ ተቋማት አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ እና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ (Health and Health Related Institutions Administrative Measure Taking and Compliant Submission Directive) በመከለስ ላይ ይገኛል። ስለሆነም ረቂቅ መመሪያዎቹ ከታች በተዘረዘሩት ማስፈንጠሪያዎች በመከተል በመመሪያዎቹ ላይ አስተያየት ያላችሁ እስከ ጥር 20 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ አስተያየታችሁን በሚከተሉት የኢሜይል አድራሻዎች መላክ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

- eden.workneh@moh.gov.et
- mesafint.abeje@moh.gov.et

Health Care Waste Management Directive:
https://docs.google.com/document/d/1yeLmqlwTxGkleD-5bDMO_DfJV5rGnauV/edit?usp=share_link&ouid=110217624369193634505&rtpof=true&sd=true

Health Institution Service Promotion:
https://docs.google.com/document/d/1UgVMD_MSCF2pyLgx1juclOyK2gcGR2T/edit?usp=share_link&ouid=110217624369193634505&rtpof=true&sd=true

Health and Health Related Institutions Administrative Measure Taking and Compliant Submission Directive:
https://docs.google.com/document/d/1wBxol-oMVcvKzdiW4OwUAd4aA7NdnuVG/edit?usp=share_link&ouid=110217624369193634505&rtpof=true&sd=true